# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት አቅራቢዎች

# አርባ አመታት



ጸሐፊው: Edward Hughes

ምሣሌ አቅራቢው: Janie Forest

ያሻሸለው (አሻሽሎ የጻፈው): Lyn Doerksen

የተተረጎመው: Abel Eshetu

አዘጋጁ: Bible for Children
www.M1914.org

©2017 Bible for Children, Inc.
ፈቃድ፡- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።



እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብፅ ምድር ባወጣቸው ጊዜ ሙሴ የሕዝቡን አምልኮ ይመራ ነበር። የምስጋና መዝሙር አዘጋጅቶም ነበር። “በክብር ከፍ ብሏልና ለእግዚአብሔር እዘምራለሁ” ብሎ ዘምሯል። እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ስላደረጋቸው ታላላቅ ነገሮች ሁሉ ሙሴ መዝሙር ተቀኝቷል።




እስራኤላውያን በምድረ በዳ
ውስጥ ሶስት ቀናት ከተጓዙ
በኋላ ተጠምተው ነበርና አንድ
ምንጭ አገኙ። ነገር ግን
ውሀው መራራ ስለነበር
መጠጣት አልቻሉም።

ከመፀለይ ይልቅ ሕዝቡ
አጉረመረሙ። ነገር ግን
እግዚአብሔር መልካም አምላክ
ስለሆነ ውሀውን ፈወሰው።







ሕዝቡ
በሁሉ ነገር
ያጉረመርሙ
ነበር። በግብጽ
እያለን የሚበላ ምግብ ነበረን፤
በዚህ ምድረ በዳ ግን በረሃብ ልናልቅ
ነው ብለው ጮሁ። በዚያ ምሽት እግዚአብሔር
ድርጭት ላከላቸው። እነርሱም ያዟቸው።



በነገታው ጠዋት ደግሞ መና ላከላቸው። መና ልክ እንደ ዳቦ የሚጣፍጥ ምግብ ነው። በየማለዳው መና መሬት ላይ ይገኝ ነበር። እንዲህ ባለ መልኩ እግዚአብሔር ሕዝቡን በምድር በዳ ይመግባቸው ነበር።

በየዕለቱ የሚበቃቸውን ምግብ ከእግዚአብሔር ዘንድ ያገኙ ነበር። አንዳንዶች ግን ከሚበቃቸው በላይ ለነገ ብለው መና ቢሰበስቡም ይበሰብስባቸው ነበር።



ምክንያቱም እግዚአብሔር ለነገ ብለው ትርፍ እንዳይለቅሙ አዘአቸው ነበርና።



ለነገ ብለው የሰበሰቡት ሁሉ ትል ያወጣ ነበር። በነገታው ሰንበት ሲሆን ብቻ ነበር ለነገ ብለው መና እንዲለቅሙ ያዘዛቸው። ነገ ሰንበት ሳይሆን የለቀሙት ሁሉ ግን ይተላ፤ይሸትም ነበር።



እግዚአብሔር እስራኤላውያን በምድረ በዳ ሲጓዙ ይንከባከባቸው ነበር።

ምግብና ውሀ ይሰጣቸው፤ከጠላቶቻቸ ውም ያድናቸው ነበር።



እስራኤላውያን
ከአማሌቃውያን ጋር
ሲዋጉ ሙሴ በትሩን
ወደ ላይ ሲያነሳ
ያሸንፉ
ነበር።





እግዚአብሔር እስራኤላውያንን
“ትዕዛዛቴን ብትጠብቁ ለእኔ የተለያችሁ
ሕዝብ ትሆናላችሁ” አላቸው።



እነርሱም ለሙሴ “እግዚአብሔር ያለንን ሁሉ
እንታዘዛለን” አሉ። ሙሴ ከእግዚአብሔር
ጋር በሲና ተራራ እየተነጋገረ ሳለ
በተራራው ስር ሆነው ይጠባበቁት ነበር።



ሙሴም በተራራው ላይ አርባ ቀናት ከእግዚአብሔር ጋር ቆየ።



እግዚአብሔርም
አስሩን ትዕዛዛት
በድንጋይ ጽላት
ላይ ጽፎ ለሙሴ
ሰጠው። ሕጉም
እስራኤላውያን
የሚተዳደሩበት
መመሪያ
ነበር።

1. ከእኔ በቀር ሌሎች አማልክት አይሁኑልህ።

2. ለተቀረጹ ምስሎች አትስገድላቸው፥ አታምልካቸው።

3. የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ።


4. የሰንበትን
ቀን ትቀድሰው
ዘንድ አስብ።
5. አባትህንና
እናትህን
አክብር።

6. አትግደል።

7. አታመንዝር።

8. አትስረቅ።

9. በባልንጀራህ ላይ በሐሰት አትመስክር።

10. ከባልንጀራህ ማናቸውንም አትመኝ።



ከእግዚአብሔር ጋር
እያለ እስራኤላውያን
አንድ አሳዛኝ ነገር
አደረጉ። አሮን ከወርቅ
ጥጃ እንዲሰራላቸው
አደረጉና በእግዚአብሔር
ፋንታ ያመልኩት
ጀመር። ከዚህም የተነሳ
እግዚአብሔር እጅግ
ተቆጣ። ሙሴም
ተበሳጨ።



ሙሴ ወደ ሰፈሩ
ሲቀርብ የወርቅ
ጥጃውንም ዘፈኑንም
አየ፤ የሙሴም ቊጣ
ነደደ፥ ጽላቶቹንም ከእጁ
ጥሎ ከተራራው በታች
ሰበራቸው። የሠሩትንም
ጥጃ ወስዶ በእሳት
አቀለጠው፥ ጥጃውን
ያመለኩትን ሁሉ በሰይፍ
ገደላቸው።

እግዚአብሔር ለሙሴ
ሌላ ሁለት ጽላቶች
ሰጠው። ከዚያም የመገናኛ
ድንኳን እንዲሰራ አዘዘው።
ይህም አጥር ያለው ትልቅ
ድንኳን ሲሆን
እግዚአብሔር
በሕዝቡ
መካከል
የሚያድርበት ነው።



ሕዝቡም በዚያ
እግዚአብሔርን
ያመልካሉ። የደመናና
እሳት አምድ የእግዚአብሔርን
ከሕዝቡ ጋር መሆን
ያሳይ ነበር።



ወደ ከነዓን ምድር ለመግባት በተቃረቡ ጊዜ ሙሴ ምድሪቷን እንዲሰልሉ አስራ ሁለት ሰዎችን ላከ። እነርሱም ምድሪቷ ምቹ እንደሆነች ተናገሩ።



የምድሪቷንም ፍሬ ይዘው ለሙሴ አመጡ። ኢያሱና ካሌብ ደግሞ በእግዚአብሔር እርዳታ ምድሪቷን እንደሚወርሱ አምነው ተናገሩ።



ሌሎቹ አስር ሰላዮች ደግሞ
የምድሪቷን ጽኑ መሆንና
የሰዎቹን ረጃጅምነት
አይተው
ስለፈሩ

“እኛ
ምድሪቷን መውረስ
አንችልም” ብለው
አጉረመረሙ።



እግዚአብሔር ከግብጽ ምድር
ሲያወጣቸው ያደረገውን
ተዓምራት ሁሉ
ረስተው
ነበር።



ሕዝቡ አስሩ ሰላዮች ያሉትን አምነው ስለፈሩ መጨህ ጀመሩ። ወደ ግብጽ ምድርም ለመመለስ ፈለጉ። ሙሴንም ሊገድሉት ፈለጉ። እግዚአብሔር ግን ሙሴን አዳነው።



ሕዝቡንም “በዚህ ምድር በዳ አርባ አመታትን
ትንከራተታላችሁ፤ ኢያሱና ካሌብ እንዲሁም
ልጆቻችሁ ግን ወደ ተስፋይቱ ምድር ይገባሉ፤
ይወርሳሉ” አላቸው።



አርባ አመታት

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል
በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

ዘጸአት ምዕ. 15
እስከ ዘሌዋውያን ምዕ. 14

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

# መጨረሻ

ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ የሚያስተምረን
ግሩም ስለሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እኛን
በመፍጠሩ እሱን እንድታውቀው ነው።

እግዚአብሔር “ኃጢአት” ብሎ የሚጠራውን ክፉ ነገር
እንዳደረግን ያውቀዋል። የኃጢአት ደመወዝ ሞት ነው
ነገር ግን እግዚአብሔር በጣም ስለወደደን አንዱንና
ብቸኛው ልጁን ለቀራኒዮ መስቀል ሞት አሣልፎ በመሥጠት
እንዲሞትና የኃጢአታችንን ዋጋ በእኛ ምትክ በመሞት
እንዲከፍል አደረገው። ኢየሱስ ከሞት ከተነሣ በኋላ
በምድር ላይ ቆይቶ ወደ ሠማይ ወደ አባቱ አረገ! ያላመንን
እኛም በኢየሱስ አዳኝት ብናምን እና ኃጢአታችንን ይቅር
እንዲል ብለምነው ይቅር ይለናል። ደግሞም ያደርገዋል።
እሱም በእኛ ውስጥ ይኖራል፤ እኛም በእርሱ ውስጥ
ለዘላለም እንኖራለን አሜን።

ይህ እውነት እንደሆነ
ካመናችሁ፣ እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት
ጌታ ኢየሱስ ሆይ አንተ አምላክ እንደሆንክ
አምናለሁ ነገር ግን ለእኔ ኃጢአት ለመሞት ስትል
ሰው ሆንህ አሁን ደግሞ ህያው ነህ። እባክህ ወደ ህይወቴ
ግባ ኃጢአቴን ይቅር በል በዚህም አዲስ ህይወት አሁን
ይኖረኛል አንድ ቀን ከአንተ ጋር ለዘልዓለም ለመኖር
ወደ አንተ እመጣለሁ። ለአንተ እንድኖርና እንደ
ልጅ እንድታዘዝልህ እርዳኝ። አሜን።

በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን በማንበብ
ከእግዚአብሄር ጋር ተነጋገር! የሐ. 3.16